የሰ/መ/ቁ. 34544

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን- ነገረ ፈጅ አቶ መስፍን ሃብቴ ይመር - ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ፋጤ ዓሊ - በሌሉበት የሚታይ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ተከፍቶ የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ጉዳይ በይግባኝ ተመልክቶ በኮ.መ.ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሰጠው ውሳኔ ላይ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የሰበር አቤቱታውን በማቅረቡ ነው፡፡

ጉዳዩ ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡ የአሁን መልስ ሰጭ በጋምቤላ ህዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሳሽ በመሆን በባለቤቷ ሞት ምክንያት በእራሷ እና የሞግዚትነት ሥልጣን ባገኘችባቸው ልጆቿ ስም ደረሰ ያለችውን ጉዳት አስልታ የጉዳት ካሣ ገንዘብ በአሁን አመልካች ላይ ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት የተነሳ የክስ አቤቱታ አቅርባለች፡፡

የአሁን አመልካችም በዚህ አኳኋን ለቀረበበት ክስ ጉዳቱ ደርሷል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ድረስ ያለው ጊዜ ሲታሰብ ሁለት ዓመት ያለፈው በመሆኑ ክሱ በይርጋ ይቋረጣል የሚለውን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ካቀረበ በኋላ ስለ ፍሬ ጉዳዩም ያለውን የመከራከሪያ ነጥቦች በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡

ክሱ በመጀመሪያ ደረጃ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ ክሱ ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሁለት ዓመት ካለፈው በኋላ የቀረበ መሆኑ ቢታወቅም ጉዳቱ ሞት ነው፤ የደረሰው ጉዳት ሞት በሆነ ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም የሚለውን ምክንያት አስፍሮ ክሱ በይርጋ ሊቋረጥ አይችልም የሚል ዳኝነት ሰጥቶ በአሁን አመልካች ላይ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ጠቅሶ የካሣ ገንዘቡን በሚመለከት ብር 30,000.00 (ሰላሳ ሺህ ብር) በርትእ እንዲከፈል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁን አመልካች ቅር ተሰኝቶ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በማቅረቡ ይኸው ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ ሙሉ ክርክር ካደረገ በኋላ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ውሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያውንም ሆነ የኃላፊነቱን ነጥብ በሚመለከት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭ በዚሁ የሰበር አቤቱታው መነሻነት ቀርባ መልስ እንድትሰጥበት ቢታዘዝም ጥሪ ደርሷት ያልቀረበች በመሆኑ ጉዳዩ በሌለችበት ታይቷል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘው ይርጋን አስመልክቶ ለቀረበው ክርክር የሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ትርጉም የሕግ መሰረት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነው፡፡

ምንም እንኳ ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ነጥብ በሚመለከት ዳኝነት ያልሰጠበት ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ ቢያስረዳም የአሁን አመልካች ለዚሁ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ያቀረበውን የይግባኝ ማመልከቻ ቅጅ እንዳየነው የይርጋ ጉዳይ በመቃወሚያነት በመጀመሪያ ደረጃው ፍ/ቤት እንስቶ የተከራከረበት መሆኑን ገልፆ ክሱ በመቃወሚያው ክርክር መቋረጥ የሚገባው ሆኖ እያለ ያለአግባብ መታለፉ ቅሬታ የፈጠረበት መሆኑን ጠቅሶ በይግባኝ የተከራከረበት ስለመሆኑ ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከክርክር አቀራረብ ሥርዓት አንፃር ይህ የሰበር አቤቱታ ደረጃውን ሳይጠብቅ የቀረበ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ወደ ተያዘው አከራካሪ ነጥብ ስንመለስ ለዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ክስ ጉዳቱ ደረሰ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ሁለት ዓመት ካለፈ በኋላ የቀረበ ለመሆኑ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ አልተገኘም፡፡ የክሱም ምክንያት ከውል ውጭ በሚደርስ ኃላፊነት ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ ይህም ከሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2143 እንደተደነገገው ማናቸውም የጉዳት ካሣ ክስ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ ካልቀረበ በቀር ክሱ በይርጋ የሚቋረጥ ነው፡፡ ካሣ የሚጠየቅበት ጉዳት ሲባል ደግሞ ሞትንም እንደሚያካትት ይኸው ሕግ በማያሻማ አኳኋን ደንግጎ እያለ፤ ክሱ የቀረበለት የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከዚህ በግልጽ ከተደነገገው ሕግ በመራቅ የሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ ጉዳት ሞት ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል አይደለም በማለት የይርጋውን ክርክር ውድቅ ማድረጉ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ቀድሞውንም ቢሆን ስለኃላፊነቱ ከማከራከሩ በፊት ክሱ በይርጋ ይቋረጣል በማለት መዝገቡን መዝጋት ሲገባው በተሳሳተ የሕግ አተረጓጎም የተነሣ የተሟላ የክስ መስማት ሂደት ማከናወኑ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## **<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የጋምቤላ ከተማ ዙሪያ ከፍተኛው ፍ/ቤት በፍት/መ/ቁ. 6/95 ግንቦት 06 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 48755 ታህሳስ 07 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የአሁን መልስ ሰጭ በአመልካች ላይ ያቀረበችው የጉዳት ካሣ ክስ ከውል ውጭ በሚደርሰው ኃላፊነት ሕግ እንደተመለከተው በሁለት ዓመት የይርጋ ጊዜ የተቋረጠ ነው ብለናል፡፡

ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት::

ቤ/ኃ